# *አለምአቀፍ ህግና ቆንስላ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል*

## I. በሰነድ ማረጋገጫ ዋና ክፍል የሚረጋገጡ ሰነዶች ማሟላት የሚገባቸው አጠቃላይ ቅድመ-ሁኔታዎች

### ማናቸውም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚረጋገጡ ሰነዶች

1. የማህተምና ፊርማ ናሙናቸው ወደ መ/ቤታችን አስቀድመው በላኩ የሚመለከታቸው ቢሮዎችና ኃላፊዎች የተረጋገጡ መሆን አለባቸው።
2. በሚመለከተው ቢሮ ተረጋግጠው ከተሰጡበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ዓመት ያላለፈባቸው አንድ ዓመት ካለፈባቸውም የታደሱ መሆን አለባቸው።
3. የሚቀርቡት ሰነዶች ዋናዎቹ /ኦሪጅናል/ መሆን አለባቸው። ፎቶኮፒዎች ተቀባይነት የላቸውም።
4. ፎቶኮፒ ለማረጋገጥ የሚያስገድድ ሁኔታ ቢያጋጥም ዋናውን ሰነድ በሰጠው አካል የተረጋገጠ (certifid copy) መሆን ይኖርበታል።
5. ለመጨረሻ ጊዜ ያረጋገጠው አካል ማህተም፣ ፊርማ እና የተረጋገጠበት ቀንና ዓመት ያሟላ መሆን ይኖርበታል። ከሶስቱ አንዱ ከጎደለ ተቀባይነት አያገኝም።
6. ቀደም ብለው በመ/ቤታችን የተረጋገጡና በተለያዩ ምክንያቶች የሚቀየሩ ወይም የሚታደሱ ከሆነ የተረጋገጡት ዋናዎቹ ሰነዶች ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል።
7. የአገልግሎት ክፍያ የሚከፈለው ለእያንዳንዱ የማረጋገጫ አገልግሎት ለሚሰጠው ሰነድ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።
8. ክፍያ የሚጠየቀው የሰነዱ ባለቤት ዜግነት መሠረት በማድረግ በመሆኑ የባለሰነዱ ሕጋዊ የዜግነት ማስረጃ ተያይዞ መቅረብ አለበት።
9. የዜግነት ማስረጃ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚኖር የቀበሌ መታወቂያ ወይም የፀና ፓስፖርት፣ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖር የፀና ፓስፖርት ወይም የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ብቻ መሆናቸው በመገንዘብ እነዚህን አሟልቶ ማቅረብ ያስፈልጋል።

## II. ከኢትዮጵያ የተለያዩ መ/ቤቶች የሚሰጡ የተለያዩ ሰነዶች ማሟላት የሚገባቸው ዝርዝር ቅድመ ሁኔታዎች

### 1. የልደት፣ ያላገባ/ች፣ የጋብቻ፣ የፍቺ፣ እና የሞት ምስክር ወረቀቶች

- ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤትና ከክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ እንዲሁም ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት የተሰጡ ሲሆን፣ በቀጥታ ይስተናገዳሉ፣
- ከብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የተለያዩ ቦታዎች የተሰጡ ከሆነ በየክልላቸው የሥራና ከተማ ልማት ቢሮዎች ወይም የፍትሕ ቢሮዎች፣
- የጥምቀትና የጋብቻ ማስረጃዎች በሀይማኖት ተቋማት የተሰጡ ከሆነ በየተቋማቱ የበላይ/ ከፍተኛ ጽ/ቤቶች፣
- ከሕክምና ተቋማት የተሰጡ የሞት ማስረጃዎች፣ በከተማ አስተዳደሩ /አዲስ አበባና ድሬዳዋ/ በክልል ጤና ቢሮ ወይም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣

  አስቀድመው ተረጋግጠው ሲቀርቡ ነው::
- የሞትና ያላገባ/ች ማስረጃዎት በሀይማኖት ተቋማት አይሰጡም፣ ቢሰጡም እንኳን ተቀባይነት የላቸውም::

### 2. የትምህርት ማስረጃዎች

- ከአዲስ አበባና ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ት/ቤቶች የተሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች በየከተሞቹ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች፣
- በብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥር ከሚገኙ የትምህርት ተቋማት የተሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች በክልሉ ትምህርት ቢሮ ወይም ስልጣን በተሰጠው የክልል ቢሮ፣
- ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲና በሥሩ ከሚገኙ የትምህርት ተቋማት የተሰጡ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሬጂስትራር ጽ/ቤት፣
- በየክልሉ ከሚገኙ ከፍተኛ የመንግስት የትምህርት ተቋማት/ዩኒቨርሲቲዎች የተሰጡ በየክልሉ በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች፣

- መንግስታዊ ካልሆኑ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተሰጡ በትምህርት ሚኒስቴር፣
- የ10ኛ/12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ምስክር ወረቀቶች በአገር አቀፍ ፈተናዎች፣
- በየክልሉ ከሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት የተሰጡ በየክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን፣

  ተረጋግጠው መቅረብ ይኖርባቸዋል።
- ከሌሎች አገሮች የተሰጡ የትምህርት ማስረጃዎችን በሚመለከት የኢትዮጵያ የአቻ ደረጃና ግመታ ማስረጃዎች ዲፕሎማና ከዛ በላይ የሆኑት በትምህርት ሚኒስቴርና ከዲፕሎማ በታች የሆኑት በየክልሉ ወይም በየከተማ አስተዳደሮች በ/አዲስ አበባና ድሬዳዋ/ ትምህርት ቢሮዎች የተሰጡ መሆን አለባቸው።

## 3. ከጤና ተቋማት የሚሰጡ የሕክምና ማስረጃዎችና ሌሎች ሰነዶች

- በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ሥር ከሚገኙ የጤና ተቋማት የተሰጡ በየከተማ አስተዳደሩ ጤና ቢሮ፣
- በብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ሥር ከሚገኙ የጤና ተቋማት የተሰጡ በየክልሉ ጤና ቢሮ ወይም ስልጣን በተሰጠው ሌላ የክልሉ ቢሮ፣
- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሥር ከሆኑት የሕክምና ተቋማት የተሰጡ ማስረጃዎች በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣

  ተረጋግጠው መቅረብ ይኖርባቸዋል።

## 4. የመንጃ ፈቃድ

- ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተሰጡ የመንጃ ፈቃዶች በፌዴራል መንጃ ፈቃድ ተቀይረው መቅረብ አለባቸው፣
- ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተሰጡ፣ የመንጃ ፈቃዶች ወይም መኪና ከመንዳት ሙያ ጋር በተያያዘ የተሰጡ ሌሎች ማስረጃዎችን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሲሆኑ በክልሉ ወይም በከተማ አስተዳደሩ /አዲስ አበባና ድሬዳዋ/ ትራንስፖርት ቢሮ፣

  ተረጋግጠው መቅረብ ይኖርባቸዋል፣

5. **የአሻራ /ከወንጀል ነፃ/ ማስረጃ**

- ማስረጃው ከፌዴራል ፖሊስ የወንጀልና የፎረንሲክ ምርመራ ቢሮ የተሰጠ መሆን ይኖርበታል።

6. **የኢትዮጵያ ፓስፖርት ኮፒ**

- የፓስፖርት ኮፒ ማረጋገጥ አስፈላጊ ሲሆን፣ ከኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ተረጋግጦ መቅረብ አለበት።

7. **የፍርድ ቤት ውሳኔ፣ ብይን፣ ትዕዛዝ የሚመለከቱ ሰነዶች**

- ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች የተሰጡ በየፍ/ቤቶቹ ሬጅስትራር ጽ/ቤቶች፣
- በብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥር በተለያዩ ደረጃዎች ከሚገኙ ፍ/ቤቶች የተሰጡ በየብሔራዊ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሬጂስትራር ጽ/ቤቶች ወይም ስልጣን በተሰጠው የክልሉ ቢሮ፣
- ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች የተሰጡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ዋና ሬጂስትራር ጽ/ቤት፣
- ከፌዴራል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍ/ቤቶች የተሰጡ በየፍ/ቤቶቹ ሬጅስትራሮች፣
- ከሸሪዓ ፍ/ቤቶች የተሰጡ በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠ/ምክር ቤት ተጋግጠው መቅረብ ይኖርባቸዋል።

8. **የውክልና፣ ዲክለራሲዮንና የቃለ-መሐላ ሰነዶች**

- ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚሰጡ፣ በከተማ አስተዳደሮቹ ደረጃ በተቋቋሙ የውልና ማስረጃ ጽ/ቤቶች፣
- ከክልላዊ መስተዳድሮች የተለያዩ ቦታዎች የተሰጡ፣ የክልል ፍትሕ ቢሮዎች ወይም የውልና ማስረጃ ጽ/ቤቶች፣

ተረጋግጠው መቅረብ ይኖርባቸዋል፣

9. **<u>የሕጋዊ ሰነዶች ትርጉም</u>**

- ትርጉሙ እንዲረጋገጥ የተፈለገ ሰነድ ዋናው ሰነድ /ኦሪጂናል/ የሚፈለግበትን ቅድመ-ሁኔታ ያሟላ መሆን ይኖርበታል።

- የሚተረጎሙ ሰነዶች ሕጋዊ የመተርጎም ፈቃድና እውቅና ባላቸው የትርጉም ድርጅቶች መተርጎም ይኖርባቸዋል፡፡
- በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ሥር ባሉ ተርጓሚዎች የተተረጎሙ ሰነዶች ከየከተማ አስተዳደሮቹ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤቶች መረጋገጥ አለባቸው፡፡
- በየብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የተለያዩ አካባቢዎች የተተረጎሙ ሰነዶች በየክልሉ ፍትሕ ቢሮዎች ወይም የውልና ማስረጃ ጽ/ቤቶች ተረጋግጠው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- እንዲረጋገጥ የተፈለገው የትርጉም ሰነድ ከዋናው ሰነድ ጋር ተያያዞ መቅረብ አለበት፡፡

## 10. <u>የንግድ ፈቃድና ንግድ ነክ ሰነዶች</u>

- ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የተሰጡ በከተማ አስተዳደሩ ንግድ ቢሮ፣
- ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክፍለ ከተሞች ከተሰጡ በየክፍለ-ከተሞቹ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤቶች ወይም ከከተማ አስተዳደሩ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ፣
- ከብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የተለያዩ አካባቢዎች የተሰጡ በየክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ወይም ስልጣን በተሰጠው ሌላ የክልል ቢሮ፣
- የወጭ ምርቶች (Export) የሚመለከቱ (የCetificate of Origin) ሰነዶች በኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት (Chamber of commerce) ወይም ስልጣን በተሰጣቸው የክልል ንግድ ምክር ቤቶች፣
- ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች የጤና፣ የኳራንቲን እና የመሳሰሉትን የሚመለከቱ ሰነዶች በግብርና እና ገጠር ልማት ሚኒስቴር እና በስሩ በሚገኙ የተለያዩ ቅርጫፍ ጽ/ቤቶች፣ ተረጋገጥው መቅረብ አለባቸው

## 11. የኢንቨስትመንት ፈቃድና ኢንቨስትመንት ነክ ሰነዶች

- ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር አካባቢ የሚመነጩ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ቢሮ፣

- ከብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የተለያዩ አካባቢዎች የተሰጡ በየክልሉ ኢንቨስትመንት ቢሮ ወይም ስልጣን በተሰጠው የክልል ቢሮ፣
- በፌዴራል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተሰጡ በሚመለከተው የመ/ቤቱ ኃላፊ፣

  ተረጋግጠው መቅረብ አለባቸው።

## 12. የጉዲፈቻ ሰነዶች

- ከአገር ውስጥ የሚመነጩ የጉዲፈቻ ሰነዶች በፌዴራል ፍ/ቤቶች የተሰጡና በፌዴራል ፍ/ቤቶቹ ዋና ሬጂስትራር ጽ/ቤት የተረጋገጡ መሆን አለባቸው።

## 13. የሐጂና ዑምራ ጉዞ እና ከዚህ ጋር የተያያዙ ሰነዶች

- ከሐጂና ዑምራ ጉዞ ጋር የተያያዘ የጉዞ ውክልና ወይም የስምምነት ሰነድ በቅድሚያ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ያወቀውና ያረጋገጠው መሆን አለበት፣
- የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ንግዱን በሚመለከት ማረጋገጥ የሚችል ቢሆንም የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ካላረጋገጠው ለብቻው ተቀባይነት የለውም።

## 14. <u>«ለሚመለከተው ሁሉ» በሚል የተዘጋጁ የመኖሪያ አድራሻ፣ የሥራ ሁኔታና ተመሳሳይ ጉዳዮችን የሚገልፁ ሰነዶች</u>

- ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቀበሌዎች የተሰጡ በየክፍለ-ከተሞቹ አስተዳደር ጽ/ቤቶች ወይም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚመለከተው ቢሮ ተረጋግጠው መቅረብ አለባቸው፣
- ከድሬዳዋ ከተማ የተሰጡ በከተማው አስተዳደር ፍትህ ቢሮ፣
- ከብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የተለያዩ ቦታዎች የተሰጡ በክልሎች ፍትሕ ቢሮ፣ ወይም ስልጣን በተሰጠው የክልል ቢሮ፣
- ከፌዴራል የመንግስት መ/ቤቶች የሚሰጡ በየመ/ቤቶቹ በሚመለከተው ኃላፊ፣ ተረጋግጠው መቅረብ አለባቸው።

## 15. ሌሎች ከዚህ በላይ ያልተገለፁና አግባብነት ያላቸው ሰነዶች

- ከተራ ቁጥር 1 እስከ 14 ከተጠቀሱት ውጭ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሰነዶች አገልግሎት ሊያገኙ የሚችሉት በሚመለከተው የመንግስት አካል ተረጋግጠው ሲቀርቡ ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፣
- መንግስታዊ ባልሆኑ የተለያዩ ተቋማት የተሰጡ ሰነዶች ለተቋሙ እውቅና ወይም ሕጋዊ ፈቃድ በሰጠው የመንግስት መ/ቤት ተረጋግጠው መቅረብ አለባቸው::

## <u>ከኢትዮጵያ ውጭ ከሌሎች አገሮች የሚመጡ ሰነዶች</u>

## 16. <u>የቀረጥ ነፃ ሰነድ</u>

- የውጭ አገር ቆይታቸውን ጨርሰው ጓዛቸውን ጠቅልለው ወደ አገራቸው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን የሚያቀርቡት የቀረጥ ነፃ ሰነድ በነበሩበት አገር ባለው የኢትዮጵያ ሚሲዮን ተረጋግጦ የተሰጠ መሆን ይኖርበታል፣
- ለዚህ አይነት ሰነድ አገልግሎት መስጠት የሚቻለው ባለመብቱ ግለሰብ በግምባር መቅረብ ሲችል ብቻ ነው:: በውክልና አይሰራም/አይፈቀድም::
- ባለመብቱ ይህንን ሰነድ ይዞ ሲቀርብ በነበረበት አገር ሲጠቀምበት የነበረና ወደ አገሩ ሲገባ የተጠቀመበት የጉዞ ሰነድ /የኢትዮጵያ ፓስፖርት፣ ሊሴፓሴ እንዲሁም ትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ/ ወይም የዜግነት ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ ይጠበቅበታል::
- የቀረጥ ነፃ ሰነዱና የዜግነት/ የጉዞ ማስረጃ ሰነዶቹ ተፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ ከዋናው ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል::

## 17. ሌሎች ከውጭ የሚመነጩ ሰነዶች

- ማንኛውም ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚገባና ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት እንዲረጋገጥ የሚፈለግ ሰነድ በቅድሚያ ሰነዱ ከመነጨበት አገር በሚገኝ የኢትዮጵያ ሚሲዮን ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የሰነዱ አመንጪ አገር ሚሲዮን ተረጋግጦ መቅረብ ይኖርበታል::

- ሰነዱ በመነጨበት አገር የኢትዮጵያ ሚሲዮን ከሌለ እንዲሁም በኢትዮጵያ የሰነዱ አመንጪ አገርን የሚወክል ሚሲዮን ከሌለ እንደአመቺነቱ የሁለቱ አገሮች ሚሲዮኖች በሚገኙበት ሌላ አገር ቀርቦ መጀመሪያ ሰነዱን ባመነጨ አገር ኤምባሲ ቀጥሎ በኢትዮጵያ ኤምባሲ መረጋገጥ አለበት፡፡
- የመንጃ ፈቃድ ከዚህ በላይ በተገለፀው አገባብ ሄዶ ለማረጋገጥ ካልተቻለ ባለጉዳዩ በራሱ መንገድ መንጃ ፈቃዱን ወደ ትራንስፖርት ባለስልጣን ይዞ በመቅረብ የተቋሙ አሰራር የሚጠይቀውን ቅድመ-ሁኔታ በማሟላት ማስቀየር ይችላል፡፡

## 18. ለሚሰጠው አገልግሎት የሚያስፈልግ ክፍያ

| ተ.ቁ | የሰነዱ አይነት | የሚጠየቀው ክፍያ | |
|---|---|---|---|
| | | ለኢትዮጵያዊ | ለውጭ ዜጎች |
| 1 | የልደት ምስክር ወቀረት | ብር 150.00 | ብር 300.00 |
| 2 | የጋብቻ ምስክር ወረቀት | » | » |
| 3 | ያላገባ/ች ምስክር ወረቀት | » | » |
| 4 | የፍቺ ምስክር ወረቀት | » | » |
| 5 | የሞት ምስክር ወረቀት | » | » |
| 6 | የትምህርት ማስረጃ | » | » |
| 7 | ከጤና ተቋማት የሚሰጡ የሕክምና እና ጤና ነክ ምስክር ወረቀቶች | » | » |
| 8 | ከወንጀል ነፃ/ የአሻራ ምስክር ወረቀቶች | » | » |
| 9 | የመንጃ ፈቃድ | » | » |
| 10 | የፓስፖርት ኮፒዎች | » | » |
| | | | |
| 1 | የፍ/ቤት ብይን፣ ትዕዛዝ፣ ውሳኔ | ብር 162.00 | ብር 324.00 |
| 2 | የውክልና ሰነዶች | » | » |
| 3 | የንግድ ሥራ ፈቃድና ንግድ ነክ ሰነዶች | » | » |
| 4 | የኢንቨስትመንት ሰነዶች | » | » |
| 5 | የቀረጥ ነፃ ሰነዶች | » | » |
| 6 | የሥራ ውል ሰነዶች | » | » |
| 7 | የጉዲፈቻ ሰነዶች | » | » |
| 8 | ዴክለራሲዮን | » | » |
| 9 | የቃለ-መሐላ ሰነዶች | » | » |
| 10 | «ለሚመለከተው ሁሉ» በሚል የተዘጋጀ ማንኛውም ሰነድ | » | » |